# ፐብሊክ ሰርቪስ ሰራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት

# የ2008 በጀት ዓመት

# የስድስት ወራት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት

**ጥር 2008 ዓ.ም**

# መግቢያ

- በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ እየታየ ያለው የትራንስፖርት አገልግሎት ችግር መንግስት ያስቀመጣቸው የመፍትሄ ሃሳቦች እንዲተገበሩ እየተደረገ ስለሚገኝ ችግሩ በመቃለል ላይ ይገኛል፡፡
- የትራንስፖርት ችግሩን ለመፍታት በመፍትሄነት በመንግስት ከተወሰዱት እርምጃዎች መካከል አንዱ ለፐብሊክ ሰርቪስ ሰራተኛው በስራ መግቢያ እና መውጪያ የተመቻቸው የትራንስፖርት አገልግሎት ነው፡፡
- የትራንስፖርት አገልግሎቱን መንግስት ባስቀመጠው አቅጣጫ ተግባራዊ ለማድረግ እንዲቻል በሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 298/2006 ፐብሊክ ሰርቪስ ሰራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡
- ድርጅቱ የተቋቋመበትን ዓላማ ከማስፈፀም ረገድ ከመስከረም 5 ቀን 2007 ዓ.ም. ጀምሮ በ55 አውቶቡሶች የትራንስፖርት አገልግሎቱን መስጠት የጀመረ ሲሆን በያዝነው በጀት አመት በስድስት ወሩ መጨረሻ ያሉት አውቶብሶች 321 በማድረስ የማጓጓዝ አቅሙን አሳድጎ በመላ የከተማዋ ክልሎች ተደራሽ ለመሆን ችሏል፡፡
- በዚህም መሰረት ድርጅቱ በ2008 በጀት ዓመት የመጀመሪያው መንፈቀ ዓመት ከመንግስት የተጣለበትን አደራ ከመወጣት ረገድ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ የፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎቱ ተደራሽ፣ ደህንነቱ የተጠበቀና ለተገልጋዩ እርካታን የፈጠረ እንዲሆን ባደረጋቸው እንቅስቃሴዎች ላይ ተጠናቀረው ሪፖርት ቀርቧል፡፡

## ክፍል አንድ

## ቁልፍ ተግባራት

| ተ.ቁ | እቅድ | ክንውን |
|---|---|---|
| 1 | የድርጅቱን እንቅስቃሴዎች በለውጥ ሰራዊት በመገንባት ሰራተኛውን በአንድ ለአምስት ለማደራጀት ይቻል ዘንድ የልማት ሰራዊት መመልመያና መገንብያ መስፈርት በበጀት አመቱ መጀመርያ ወር ማዘጋጀት፣ | የልማት ሰራዊት መመልመያና መገንብያ መስፈርት ተዘጋጅቶ በነሀሴ ወር ለሁሉም ስራ ሂደት የተሰራጨ ሲሆን አፈጻጸሙም 100 % ሊሆን ችሏል፡፡ በዚህም መመርያውን መሰረት አድርገው ግንባር ቀደም እንዲመለምሉና የለውጥ ሰራዊቱንም እንዲያደራጁ ተደርጓል፡፡<br><br>በዚህም የለውጥ ሰራዊት ሚና በድርጅቱ እንቅስቃሴዎች ላይ የሚያስገኘው ጠቀሜታ የቀረበ ሲሆን መላው ሰራተኛም በተሰጠው የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት በቡድን የመደራጀትና በዚህም አግባብ ስራዎችን በመስራት በሁሉም የስራ ሂደቶች የሚገኙ ሰራተኞች በየስራ ሂደታቸው በአንድ ለአምስት እንዲደራጁ ተደርጓል፡፡ |
| 2 | በግማሽ አመቱ 154 1ለ5 አደረጃጀቶችን መፍጠርና ማጠናከር፣ | አደረጃጀት ለመፍጠር በተያዘው እቅድ መሰረት በስድስት ወራቱ ወስጥ 149 የአንድ ለአምስት ቡድኖችን የማደራጀት ስራዎች ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡ በዚህም እቅድ ክንውኑ 97% ሊሆን ችሏል፡፡ |
| 3 | የ1 ለ5 ቡድን አደረጃጀቶች በተቀረፀው አጀንዳ መሠረት የሚደረጉትን ውይይቶች በየሳምንቱ በመከታተል አፈፃፀሙን ሪፖርት ማድረግ፣ | በበጀት ዓመቱ ባለፉት 24 ሳምንታት በተደራጁ የአንድ ለአምስት ቡድኖች በቃለ ጉባዔ የተደገፈ ተከታታይነት ያላቸው ሳምንታዊ ውይይቶች የተደረጉ ሲሆን ስለአፈፃፀማቸው ተገቢው ክትትልና የሱፐርቪዥን ስራዎች ከመሰራታቸውም በላይ ሳምንታዊ ሪፖርቶች ቀርበዋል፡፡በዚህም ክንውኑ ከዕቅዱ ሲነፃፀር 97% አፈፃፀም አለው፡፡ |
| 4 | በየሥራ ሂደቱ በተደራጁ የአንድ ለአምስት ቡድን ሰብሳቢዎች ጋር በየ 15 ቀኑ ውይይት ማካሄድ፣ | በየሥራ ሂደቱ በተደራጁ የአንድ ለአምስት ቡድኖች የሚገኙ የየቡድኑ ሰብሳቢዎች ጋር በ15 ቀኑ በስራ ሂደት ኃላፊዎች ሰብሳቢነት በእያንዳንዱ የ1 ለ5 ቡድን በተደረጉ ዋና ዋና የመወያያ ርዕስ፣ በተከሰቱ ችግሮች፣ እና በቡድን ደረጃ ለመፍታት ባልተቻሉ ችግሮች ዙሪያ ውይይቶች ተደርገዋል ችግሮችንም ለመፍታት ጥረት ተደርጓል፡፡ |
| 5 | 15 ግንባር ቀደሞችን በመመልመል አንድ የግንባር ቀደሞች ፎረም ማቋቋም፣ | በዕቅድ አፈጻጸም ውጤታቸውና በአርአያነታቸው እንዲሁም በተቀመጡ መስፈርቶች የተመለመሉ 15 ግንባር ቀደሞችን የያዘ አንድ የግንባር ቀደም ፎረም የተመሰረተ ሲሆን እቅድ ክንውኑም 100% ሊሆን ችሏል፡፡ |

| ተ.ቁ | እቅድ | ክንውን |
|---|---|---|
| 6 | የሚደረጉ የ1ለ5 ውይይቶች ችግር ፈቺ መሆናቸውን በክትትልና ድጋፍ ማረጋገጥ | በሁሉም ስራ ሂደቶችና ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በተፈጠሩ የለውጥ ሰራዊት ቡድኖች አደረጃጀትና ውይይቶች ውጤቶች እየተመዘገቡ መምጣት የቻሉ ሲሆን ችግሮችን በአንድ ለ አምስት ውይይት ፕሮግራም የመፍታት፣የአመለካከት ለውጥ መታየታቸው እንዲሁም ሰራተኞች በለውጥ ሰራዊት አቅማቸው መገንባት መቻሉ በተደረጉ የሱፐርቪዥን ስራዎች ከታዩት ውጤቶች መካከል ናቸው፡፡ |
| 7 | የለውጥ እና የመልካም አስተዳደር ስራዎች መከታተያ ቼክ ሊስት በማዘጋጀት ሱፐርቪዥን በማካሄድ የተገኘውን ውጤት በየወሩ ሪፖርት ማድረግ | ለውጥ ስራዎችን ከመከታተል ረገድ የ1ለ5 ቡድኖች መከታተያ ቼክ ሊስት በማዘጋጀት የሱፐርቪዥን ስራ በየሳምንቱ በማካሄድ ሪፖርት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡<br>በዚህም<br>የለውጥና የመልካም አስተዳደር ስራዎች በመከታተልና በመደገፍ የሚደረጉ የ1ለ5 ውይቶች አስቸኳ ይሁኔታ ካልገጠመ በቀር እንዳይቆራረጡ የማድረግ ስራ በመስራ ት ለይ ይገኛል፡፡ |
| 8 | በየሩብ ዓመቱ ከተገልጋዮች ጋር የምክክር መድረክ መፍጠር | ከድርጅቱ ስራ ጋር ተያያዥነት ያላቸውና በትስስር ሊሰሩ የሚገባቸውን ድርጅቶች በመለየት 400 አባላት ያሉት የሕዝብ ክንፍ በማደራጀት፣ በየሶስት ወሩ የውይይት መድረክ በማዘጋጀት ከተገልጋዮች ጋር ውይይት ማድረግ ተችሏል፡፡<br>በስድስት ወሩ ውስጥ ለሁለት ግዜ በድርጅቱ የትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ እና መልካም አስተዳደር ችግሮች ጋር በተያያዘ ውይይት ማካሄድ ተችሏል በዚህም የተቀመጠውን እቅድ 100% ማከናወን ተችሏል፡፡ |
| 9 | የውጤት ተኮር /BSC/ ጥናት ማካሄድና በተቋምና በስራ ሂደት ስታንዳርድ ከጥቅምት እስከ ጥር ባሉት ግዚያት ተግባራዊ ማድረግ፡፡ | የውጤት ተኮር ስርአት /BSC/ አመራሩ ተመሳሳይ ግንዛቤ እንዲኖረው ከፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ሚንስቴር አሰልጣኝ እንዲመደብ በማድረግ 63 ሰራተኞች ስልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል፡፡<br><br>በዚህም የድርጅቱን ሥራዎች በዕቅድ ላይ በተመሰረተ መልኩ ውጤቱን ለመገምገም እንዲቻል የውጤት ተኮር ጥናት ሰነድ በድርጅት ደረጃ በተያዘው የግዜ ገደብ የተዘጋጀ ሲሆን በዚሁ ሰነድ ላይ በመመስረት የተቋም፣ የስራ ሂደቶች እና የሰራተኛው ውጤት ተኮር /BSC/ መመዘኛ የማዘጋጀት ሂደት ተጀምሯል፡፡ |
| 10 | በሁለተኛው ሩብ አመት በካይዘን ፍልስፍና ስራ ሂደቶች ስልጠና መስጠት፡፡ | በካይዘን ፍልስፍና ላይ ስልጠና ለመስጠት በጥር እና ታህሳስ የታቀደ ሲሆን በመስከረምና ህዳር ወር ለ 190 ሰራተኞች ስልጠና የመስጠት ስራ ተሰርቷል ከዚህም በተጨማሪ በንብረት ክፍል ፣በኤሌክትሪክ እና በመዝገብ ቤት በአምስቱ "ማ"ዎች ዙሪያ የሙከራ ትግበራ በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡ |

| ተ.ቁ | እቅድ | ክንውን |
|---|---|---|
| 11 | የተገልጋዮች ቅሬታ የሚቀርብበትን ስርአት እስከ ሰኔ መዘርጋት፣ | ተገልጋዩም ሆነ ሰራተኛው ቅሬታ የሚያቀርብበትን ስርአት የመዘርጋት ስራ 90% ቱ የተከናወነ ሲሆን የቅሬታ አፈታት መመሪያ ረቂቅ ተዘጋጅቶ ለውይይት ቀርቧል፡፡ |
| 12 | የዜጐች ስምምነት ሰነድ/ የዜጎች ቻርተር በሁለተኛው ሩብ አመት ተግባራዊ ማድርግ | የዜጎች ቻርተር ተዘጋጅቶ እና በህዝብ ክንፉ ውይይት ተደርጎበት በማጽደቅ በስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡ በዚህም ክንውኑ ከዕቅዱ ሲነፃር 100% አፈፃፀም አለው፡፡ |
| 13 | የሥራ ቡድኖች ስምምነት ሰነድ /Team Charter/ በሁለተኛው ሩብ አመት ተግባራዊ ማድርግ፡፡ | የስራ ቡድኖች የሥምምነት ቻርተር/Team charter/ በሁሉም የስራ ሂደቶች እንዲዘጋጅ በማድረግ ፀድቆ በሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡ የተያዘው እቅድም 100% ሊከናወን ችሏል፡፡ |
| 14 | በፈጻሚውና ለባለድርሻ አካላት የእቅድ ትውውቅ የአፈጻጸም የግምገማ መድረኮችን በየሩብ አመት ማከናወን፣ | አጠቃላይ የድርጅቱን ሰራተኛ እና ባለድርሻ አካላት ባሳተፈ መልኩ በድርጅቱ አመታዊ እቅድ ፣ የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ፣ በመልካም አስተዳደር ችግሮችና አፈታታ ዙርያ በተለያየ ግዜ የማወያየት ስራ ተሰርቷል |
| 15 | የትንስፖርት አገልግሎት ዙርያ አገልግሎት አሰጣጡን ያማካለ የደሳ ጥናት የማካሄድ | ከ 2500 በላይ መጠይቅ በማዘጋጀት ከእያንዳንዱ የአውቶቡስ ተሳፋሪ ላይ በተወሰደ የተገልጋይ ናሙና በተዘጋጀ መጠይቅ በአገልግሎት አሰጣጥ፣ በባስ ካፕቴኖች የሥነ ምግባር እና በመነሻና መድረሻ ሰዓት ዙሪያ አስተያየቶችን በመሰብሰብ ጎልተው በወጡ ችግሮች ላይ ወቅታዊ እርምጃዎች ተወስደዋል፡፡ |
| 16 | በድርጅቱ የተለዩ የመልካም አስተዳደር ችግሮች የሚፈቱበትን ዘዴ በአንደኛዉ ሩብ ዓመት በመለየት ተግባራዊ ማድረግ | በድርጅቱ የመልካም አስተዳደር ችግሮች በሁለተኛው ሩብ አመት ተለይተዋል ለመፍታት የሚያስችል ዕቅድና የድርጊት መርሃ ግብር ተዘጋጅቷል፡፡<br>በተዘጋጀው ዕቅድ ላይ ፈፃሚው/ የድርጅቱ ሰራተኛ እንዲወያይበት በማድረግ ፀድቋል፡፡<br>እያንዳንዱ የመልካም አስተዳደር ችግር ላይ የሚመለከተው የስራ ሂደት ተለይቷል፡፡<br>የዕቅዱን አፈፃፀም ተግባራዊነት የሚከታተል ኮማንድ ፖስት እንዲቋቋም የማድረግ ስራ በመሰራት ላይ ይገኛል ፡፡<br>የተለዩትን የመልካም አስተዳደር ችግሮች ለመፍታት በተደረገው እንቅስቃሴ ችግር ተብለው የተለዩትን የመፍታት ተግባር በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡ |

## ክፍል 2
## <u>አበይት ተግባራት</u>

### 2.1 ትራንስፖርት አስተዳደር

#### <u>ፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎት</u>

- ☐ በግማሽ ዓመቱ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ለሚገኙ ለ8,321,000 የፌደራልና አዲስ አበባ ከተማ የፐብሊክ ሰርቪሲ ሰራተኞችን በ410 አውቶቡሶች ለማጓጓዝ ታቅዶ በአማካኝ በተሰማሩ 321 አውቶብሶች 5,305,996 ሰራተኞችን በደርሶ መልስ የተጓጓዙ ሲሆን አፈፃፀሙ ከእቅዱ ጋር ሲነፃፀር 64% አፈጻጸም አለው፡፡

- ☐ በግማሽ ዓመቱ ውስጥ የተጓጓዛ ተሳፋሪ መጠን አንሶ የታየው አውቶብሶች እስከ ህዳር ወር 2008 ዓ.ም ድረስ ተጠናቀው ይገባሉ ተብሎ ታሳቢ በመደረጉና አውቶብሶች በወቅቱ ባለመግባታቸው ምክንያት ሲሆን በተለይም እስከ መጀመርያው ሩብ አመቱ መጨረሻ ድረስ አገልገሎት ይሰጥ የነበረው በ199 አውቶብስ መሆኑ አፈጻጸሙን ዝቅ ሊያደርገው ችሏል፡፡

- ☐ በስድስት ወሩ የተሳፋሪ ብዛት በየሩብ አመቱ ተከፍሎ በንጽጽር ሲታይ በመጀመሪያው ሩብ ዓመት የተሳፋሪ ብዛት 2,334,374 ሲሆን በ2ኛው ሩብ ዓመት ደግሞ 2,971,622 ነው ፡፡ በዚህም መሰረት በ2ኛው ሩብ ዓመት የተጓጓዘው ተሳፋሪ ከመጀመሪያው ሩብ ዓመት ተሳፋሪ በ637,248 ወይም በ27.3% ብልጫ አሳይቷል፡፡ ለዚህም መንስዔው የአውቶቡሶች ቁጥር በመጨመሩ እና አገልግሎቱን ተደራሽ ለማድረግ መነሻ መስመሮች ከ27 ወደ 42 እንዲሁም መዳረሻ መስመሮች ከ11 ወደ 17 እንዲያድጉ በመደረጉ ነው፡፡

- ☐ በግማሽ ዓመቱ በደርሶ መልስ ጉዞ 2,130,000 ኪ.ሜ ርቀት ለመሸፈን ቢታቀድም በጠቅላላው በአማካይ በተሰማሩት 321 አውቶቡሶች በአራቱም ቅርንጫፎች 1,342,858 ኪ.ሜ ወይም የዕቅዱ 63% ተከናውኗል፡፡

- ☐ ሽፋኑ ከዕቅዱ ሊቀንስ የቻለው ከላይ በተገለጸው ምክንያት ይሰማራሉ ተብለው በዕቅድ የተያዙት አውቶቡሶች በተሟላ ሁኔታ ባለመሰማራታቸው ነው፡፡

#### <u>የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት</u>

- ☐ በአዲስ አበባ ከተማ ውስት በቀን በምሽት እና ቅዳሜ የእረፍት ቀን በተመጣጣኝ ክፍያ በተሰጠው የትራንስፖርት አገልግሎት በግማሽ ዓመቱ 156 አውቶቡሶችን በማሰማራት ለ6,829,000 ተሳፋሪዎችን ለማጓጓዝ ታቅዶ በአማካኝ 157(101%) አውቶቡሶችን በማሰማራት ለ2,153,951 አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡በዚህም መሰረት የተጓጓዘ ተሳፋሪ ከዕቅዱ ጋር ሲነፃፀር 31.5% አፈጻጸም አለው፡፡

- ☐ በአገልግሎቱ የተሰማሩ አውቶቡሶች ከዕቅድ በላይ ቢሆንም በተሳፋሪ ረገድ ቀንሶ የተገኘበት አብይ ምክንያት በአብዛኛው አገልግሎቱ በአንድ አቅጣጫ ብቻ ማለትም በተመላሽ ጉዞ የተሳፋሪ ቁጥር በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ፣ ህብረተሰቡ አውቶብስን ለመጠቀም ያለው ፍላጎት አነስተኛ በመሆኑ እንዲሁም አውቶብሶቹ የሚሰጡትን የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ያለመረዳት ሁኔታዎች መኖራቸው የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

- ☐ ከዚህ አንጻር የተጠቃሚውን ቁጥር ከፍ ለመድረግ የተሰሩ የማስታወቅያ ስራዎች ዝቅተኛ ቢሆኑም በታህሳስ ወር ጀምሮ በሚድያና በተለያየ ዘዴ የማስታወቅያ ስራ መስራት ተችሏል ፡፡

<u>የኮንትራት አገልግሎት</u>

- ☐ ከተለያዩ መ/ቤቶች ለአጭር ጊዜ በሚቀርብ የኮንትራት ትራንስፖርት አገልግሎት በመስጠት ለድርጅቱ ተጨማሪ ገቢ ለማግኘት በግማሽ ዓመቱ በ60 አውቶቡሶች 3,000 ለማጓጓዝ ቢታቀድም በ88 አውቶቡሶች (146%) በማሰማራት በጠቅላላው 4,590 ተሳፋሪዎች ተጓጉዘዋል፡፡

- ☐ በዚህም መሰረት በስድስት ወሩ የተጓጓዘው ተሳፋሪ ከዕቅዱ ጋር ሲነፃፀር 153% አፈፃፀም አለው፡፡ ክንውኑ ከዕቅዱ በልጦ የተገኘበት ምክንያት ድርጅቱ በኮንትራት የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ መሆኑ በበርካታ ድርጅቶች እየታወቀ በመምጣቱ ተደጋጋሚ የኮንትራት ጥያቄዎች እየቀረቡ የትራንስፖርት አገልግሎት በመሰጠቱ ነው ፡፡

<u>የሊዝ ትራንስፖርት አገልግሎት</u>

- ➢ ከሶስት ድርጅቶች ጋር ሰራተኞቻቸውን ከየመኖሪያ አካባቢያቸው ወደ ስራ ቦታቸው ለማጓጓዝ በተደረገው የረዥም ጊዜ የሊዝ አገልግሎት በ6 ወሩ ውስጥ በ15 አውቶቡሶች 180,000 በምልልስ ለማጓጓዝ ታቅዶ ክንውኑ በ9 አውቶቡሶች ለ155,402 ተገልጋዮች አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡ ይህም በተጓጓዥ ረገድ የእቅዱ 86% ነው፡፡

- ➢ ለክንውኑ ከዕቅዱ ማነስ መንስዔው በተለይም የአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን የተከራያቸውን አውቶቡሶች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ በመምጣቱ ነው፡፡

<u>የሚይንቴናንስና እንጂነሪንግ</u>

**አጠቃላይ የጥገና አፈፃፀም**

- ☐ የድርጅቱ አውቶብሶች ደህንነታቸው ተጠብቆ የሚፈለግባቸውን አገልግሎት እንዲሰጡ ከማድረግ ረገድ በመጀመርያው መንፈቅ አመት በቁጥር 58,385 የሚሆኑ የመጀመሪያ ደረጃ የመከላከል ጥገና (Type A maintenance) በሁለተኛ ደረጃ የመከላከል ጥገና

(Type B maintenance) እንዲሁም በአለታዊ እና ሳምንታዊ ፍተሻ ስራዎች ለማድረግ በእቅድ ተይዞ በድምሩ 44,352 ጥገናዎችን ማከናወን ተችሎዋል ፡፡ በዚህም መሰረት ክንውኑ ከእቅዱ ጋር ሲነጻጸር 76% አፈጻጸም አለው፡፡

- የአፈጻፀሙ ከእቅዱ ያነሰበት ምክንያት ትራንስፖርት አገልግሎቱ ከሀምሌ ጀምሮ በየወሩ የ42 አዉቶብሶች ርክክብ ይፈጸማል ተብሎ ታሳቢ በማድረግ እቅድ የተዘጋጀ ሲሆን በተቀመጠው እቅድ መሰረት የአውቶብሶች መቅረብ አለመቻላቸው አፈጻጸም ላይ ዝቅ እንዲል አድርጓል፡፡

## የትራፊክ አደጋ /የአውቶቡሶች ግጭት/

- ባለፉት 6 ወራት የተመዘገቡ 207 የመንገድ ላይ ትራፊክ አደጋ በድርጅቱ አውቶብሶች ላይ የደረሰ ሲሆን 53 ቱ ከባድ እና 154 ቀላል የትራፊክ አደጋዎች ናቸዉ፡፡
- ከደረሱት አጠቃላይ አደጋዎች በመጀመርያው ሩብ አመት 74 አደጋዎች የደረሱ ሲሆን 50 ቀላልና 24ቱ ደግሞ ከባድ አደጋዎች ነበሩ ፡፡ በሌላ መልኩ በሁለተኛው ሩብ አመት የአደጋ ቁጥር ጨምሮ የታየ ሲሆን ይህም ከባድ 29 እና ቀላል 104 ሆኖ በድምሩ 133 አደጋ ተመዝግቧል፡፡
- ለዚህም ግጭት ቁጥር መጨመር እንደምክንያትነት የሚጠቀሱት አደጋን ተከላክሎ ከማሽከከር ረገድ በባስ ካፕቴኖች ዙርያ ክፍተት መኖሩ ፣ በከተማው የሚስተዋለው የትራፊክ መጨናነቅ እንዲሁም የተሰማሩት አውቶብሶች ቁጥር ከመጀመርያው ሩብ አመት አንጻር መጨመሩ የግጭቱ አሃዝ ከፍ እንዲል አድርጎታል፡፡
- በስድስት ወር ውስጥ ለአደጋው መድረስ እንደምክንያትነት የተቀመጠው 143 አደጋዎች በድርጅቱ ባስ ካፕቴኖች ስህተት እንደሁም 64 በ 3ተኛ ወገን ምክንያት ነው፡፡
- ስለሆነም ይህን የአደጋ ቁጥር ለመቀነስ ያስቸል ዘንድ ለ 450 ባስ ካፕቴኖች አደጋን ተከላክሎ ስለማሽከርከር ስልጠናዎች ለመስጠት በእቅድ ተይዞ በድምሩ ለ 453 የድርጅቱ ባስ ካፕቴኖች ስልጠናዎች የተሰጠ ሲሆን አፈጻጸሙም (101%) ሊሆን ችሏል፡፡

## ሎጂስቲክና ሰፕላይ

አቅርቦት

- ለድርጅቱ የስራ እንቅስቃሴ የሚውሉ ግብአቶች፣ መገልገያዎች እና ቋሚ ንብረት ግዢ ለማከናወን በግማሽ አመቱ ውስጥ በድምሩ 705,802,578 ብር የሚያወጣ ግዥ ለመፈፀም እቅድ የተያዘ ሲሆን ክንውኑ ብር 533,208,747.35 ግዥ ተፈፅሟል በዚህም

መሰረት ክንውኑ ከእቅዱ ጋር ሲነጻጸር አፈፃፀሙም 75.60% ነው። ከዚህ ውስጥ ትልቁን ድርሻ የያዙት ፦ ለአውቶብስ ግዥ 512,693,669 እና ለነዳጅ ግዢ የዋለ ብር 14,623,652 ይገኙበታል።

<u>የሰው ኃብት ልማትና አስተዳደር</u>

- ☐ በግማሽ አመቱ መጨረሻ ላይ በድርጅቱ ያለው ጠቅላላ የሰው ሀይል 1018 ሲሆን ከዚህም መካከል ወንድ 812፣ ሴት 206 ነው።
- ☐ በድርጅቱ ካሉት አጠቃላይ ሰራተኞች በቋሚነት ቅጥር የተፈጸመባቸው ሰራተኞች ብዛት 574 ሲሆኑ የኮንትራት ሰራተኞች ብዛት 444 ነው።

<u>በግማሽ ዓመቱ የተቀጠሩ እና የለቀቁ ሰራተኞች</u>

- ☐ በ6 ወሩ ቅጥር ለመፈፀም በዕቅድ ከተያዘው 286 ሰራተኞች ቅጥር የተፈፀመባቸው 140 ሰራተኞች ሲሆኑ ይህም በዕቅድ ከተያዘው አንፃር 49% ማከናወን ተችሏል።ለእቅዱ አፈጻጸም ማነስ በምክንያትነት በምክንያትነት ከተቀመጡት ምክንያቶች መካከል፦
  - ✓ በመዋቅር አደረጃጀቱ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት የሰው ሃይል አለመገኘቱ
  - ✓ ከምዝገባ እስከ ቅጥር ያለው የቅጥር ሂደት ረዥም ግዜ መውሰድ መቻሉ
  - ✓ በከተማው እየተፈጠሩ ባሉት ሰፊ የስራ እድሎች ምክንያት የሰራተኛ ፍሰት መኖሩ ናቸው።
- ☐ በሌላ መልኩ ከድርጅቱ በ6 ወሩ ውስጥ ከነበሩት ሰራተኞች 105 የለቀቁ ሲሆን በራስ ጠያቂነት 83 ሰራተኛ (79%)፣በጡረታ 13 ሰራተኛ (13%) ፣2 ሰራተኞች በሞት እንዲሁም በዲስፕሊን 7 ሰራተኛ (7%) ከደርጅቱ ለቀዋል።

<u>ኮርፖሬት ፋይናንስ</u>

- ❑ የድርጅቱ የ2007 ዓ.ም በጀት ዓመት ሂሳብ ተዘግቶ በኦዲት አድራጊው የኦዲት ሰርቪስ ኮርፖሬሽን ድርጅት እየተመረመረ ይገኛል።
- ❑ የመንግስት ግዴታዎች ማለትም ቫት፣ የሥራ ግብር ፣የጡረታ መዋጮ፣እና የአገልግሎት ተቀናሾች በአዋጅ መሠረት ለሚመለከተው አካል ተከፍሏል።

ፋይናንስ ዘርፍ እንቅስቃሴ

<u>አጠቃላይ ገቢ</u>

- ☐ ድርጅቱ በመንፈቅ ዓመቱ ከተለያዩ የገቢ ርዕሶች በድምሩ 123,540,381.00 ገቢ ለማግኘት በእቅድ የተያዘ ሲሆን በጠቅላላው ብር 44,735,891.00 ወይም የእቅዱን

36% ተከናውኗል፡፡ የወሩ ጠቅላላ ገቢ ከእቅድ አንፃር ሲገመገም አንሶ የታየው ለህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሲሰጥ ለሚደርስ ኪሳራ ማካካሻ ይሆናል ተብሎ ለድጎማ በእቅድ የተያዘው ብር 57,499,998.00 በተሰብሳቢ ባለመመዝገቡ ነው፡፡

**በሌላ በኩል በመንፈቅ ዓመቱ ውስጥ የተገኘው ጠቅላላ ገቢ በዋና ዋና የገቢ ርዕሶች ሲተነተን፣**

- ከኮንትራት አገልግሎት -------------------------------------ብር 401,269.00
- ከፐብሊክ ሰርቪስ አገልግሎት -----------------------------ብር 33,349,944.00
- ከሊዝ ትራንስፖርት አገልግሎት---------------------------ብር 4,280,536.00
- ከሃይገር መለዋወጫ ሽያጭ---------------------------------ብር 530,984.00
- ከህዝብ ትራንስፖርትአገልግሎት----------------------------ብር 5,273,864.00
- ከሱቅ ኪራይና ሌሎች ገቢዎች-----------------------------ብር 898,908.00 ነው፡፡

- በአጠቃላይ የመንፈቅ ዓመቱ አጠቃላይ ገቢ ውስጥ 76% ከፐብሊክ ሰርቪስ አገልግሎት፣10% ከሊዝ ትራንስፖርት አገልግሎት 12% ደግሞ ከተማ ውስጥ የህዝብ ትራንስፖርትና ከኮንትራት አገልግሎት የተገኘ ሲሆን ቀሪው 2% ደግሞ ከሱቅ ኪራይና ሌሎች ገቢዎች የተገኘ ነው፡፡
- በሌላ በኩል ከፐብሊክ ሰርቪስ አገልግሎት ተብሎ የተገለጸው ብር 33,349,944.00 አገልግሎት ተሰጥቶ ገንዘቡ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር እና አ/አበባ ከተማ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ያልተሰበሰበ ነው፡፡

### የገቢዎች ዝርዝር መግለጫ

<u>የኮንትራት አገልግሎት ገቢ</u>

- ድርጅቱ በመንፈቅ ዓመቱ ለተለያዩ ድርጅቶች የኮንትራት አገልግሎት በመስጠት በድምሩ ብር 401,269.00 ገቢ አግኝቷል፡፡
- የተገኘው ገቢ በመንፈቅ ዓመቱ ከተያዘው ዕቅድ ብር 300,000.00 ጋር ሲነፃፀር 136% አፈፃፀም አለው፡፡
- ይህም አፈጻጸም ከፍ ብሎ የታየው ከጊዜ ወደ ግዜ የትራንስፖርት አገልግሎቱን እያወቁ ያሉ ድርጅቶችና የህብረተሰብ ክፍሎች እየጨመረ በመምጣታቸው የተጠቃሚ ቁጥር መጨመር በመቻሉ ነው፡፡

<u>የከተማ ውስጥ የሊዝ አገልግሎት</u>

- ድርጅቱ በመንፈቅ ዓመቱ የከተማ ውስጥ የሊዝ አገልግሎት በመስጠት ብር 6,316,000.00 ገቢ ለማግኘት በዕቅድ በመያዝ ብር 4,280,536.00 ወይም የእቅዱን 68% ሲሆን በዚህም የተሻለ አፈፃፀም ቢኖርም በእቅድ ከተያዘው አንጻር ሲታይ አፈጻጸሙ ዝቅ ብሎ የታየው የሊዝ አገልገሎት ይጠቀሙ የነበሩት ድርጅቶች

የራሳቸውን ተሽከርካሪዎች በመግዛት እና በመሳሰሉት ምክንያት ይጠቀሙ የነበሩትን የአውቶብስ መጠን በመቀነሳቸው ምክንያት ነው ፡፡

## የከተማ ወስጥ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት

- ድርጅቱ በመንፈቅ ዓመቱ የከተማ ውስጥ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት በመስጠት ብር 7,128,000 ለማግኘት እቅድ በመያዝ ብር 2,615,675 ወይንም የእቅዱን 37% ማከናወን ተችሏል፡፡
- ለዚህም አፈጻጸም ማነስ ህብረተሰቡ የታክሲ አገልግሎቱን እንዲጠቀም ከማድረግ ረገድ በቂ የማስተዋወቅ ስራ ባለመሰራቱ ሲሆን ከዚህ አንጻር የተጠቃሚውን ቁጥር ከፍ ለመድረግ የተሰሩ የማስታወቅያ ስራዎች ዝቅተኛ ቢሆኑም በታህሳስ ወር ጀምሮ በሚድያና በተለያየ ዘዴ የማስታወቅያ ስራ መስራት ተችሏል ፡፡

## የሃይገር ሚዲባስ መለዋወጫ ሽያጭ

- ድርጅቱ በመንፈቅ ዓመቱ የሃይገር ሚዲባስ ተሽከርካሪዎች መለዋወጫ ሽያጭ በማከናወን ብር 530,984.00 ማግኘት የተቻለ ሲሆን በሩብ ዓመቱ ይገኛል ተብሎ በእቅድ ከተያዘው ብር 499,998.00 ጋር ሲነፃፀር አፈፃፀሙ 106% ነው፡፡
- ለዚህ ከፍተኛ አፈጻጸም ምክንያት ባሳለፍነው ስድስት የተደረገ የዋጋ ማስተካከያን ተከትትሎ አቅርቦቱን የሚፈልግ የደንበኛ ቁጥር በመጨመሩ ነው፡፡

### አጠቃላይ ወጪ

## ኦኘሬሽናል እና አስተዳደራዊ ወጪዎች

## ኦኘሬሽናል ወጪዎች

- ድርጅቱ በመፈቅ ዓመቱ ለተለያዩ ኦፐሬሽናል ወጪወች ብር 147,483,461.00 ወጪ ለማድረግ በእቅድ የተያዘ ሲሆን በጠቅላላው ብር 121,622,992.00 ወይም የእቅዱ 82% ተከናውኗል፡፡
- ከዚህም አንፃር በመንፈቅ ዓመቱ ከታየው ጠቅላላ ወጪ ውስጥ ትልቁን ድርሻ የያዘው፡-
  - የእርጅና ቅናሽ --- ------------------------------------------..ብር 79,345,820.00
  - የሠራተኛ ደሞዝና ተያያዥ ወጪዎች----------------------ብር 16,712,266.00
  - መለዋወጫ ---------------------------------------------------- ብር 1,220,644.00
  - ነዳጅ ዘይትና ቅባት ----------------------------------- ------- ብር 13,217,374.00
  - ኢንሹራንስ------------------------------------------------------------ብር 9,606,199.00

ሌሎች ወጪዎች ብር1,073,019.00 ሲሆን ለኪራይ ብር 447,670, ለመብራት ብር 95,197, እና ሌሎች ተካተዋል ፡፡

## አስተዳደራዊ ወጪዎች

- ድርጅቱ በግማሽ ዓመቱ ውስጥ ለተለያዩ አስተዳደራዊ ወጪወች 18,304,966.00 ወጪ ለማድረግ በእቅድ የተያዘ ሲሆን በጠቅላላው ብር 9,584,407.00 ወይም የእቅዱ 52%ተከናውኗል፡፡

በመንፈቅ ዓመቱ ከታየው ጠቅላላ ወጪ ውስጥ ትለቁን ድርሻ የያዘው፡-

- የሰራተኛ ደሞዝና ተያያዥ ወጪዎች--------------------ብር 4,772,436.00
- የጽህፈት መሳሪያና የቢሮ እቃዎች ግዥ-----------------ብር 541,914.00
- የአስፋልት ጥገና ወጪ-------------------------------------ብር 1,438,807.00
- ኢንሹራንስ -------------------------------------------------ብር 1,154,904.00
- የቅ/ፍ አገልግሎት መስጫ ቅ/ፍ ጽ/ቤት ኪራይ……….447670.00ብር
- ለድርጅቱ በአል ወጪ የተደረገ …………………..431,419.00 ብር ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 200,000 በስፖንር መሸፈን ተችሏል፡፡

በሌላ መልኩ፡-

- ለማስታወቅያ ……………………….84,763.00 እንዲሁም
- ለህክምና ወጪ …………………….55,125.00ተካተዋል፡፡

**ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳቦች፣**

**ተሰብሳቢ ሂሳብ**

በድርጅቱ በአጠቃላይ ከቀድሞው ዋልያ አገር አቋራጭ አውቶቡስ አገልግሎት ድርጅት የዞረውን ጨምሮ ከረዥም ጊዜ ቆይታቸው አኳያ መረጃ ሊገኝላቸው ያልቻሉና መሠብሰብ ያልቻሉ በድምሩ ብር 1,424,510.18 ተሰብሳቢ ሂሳብ ያለ ሲሆን መሠብሰብ ያልቻሉት ሂሳቦች እንዲሠረዙ በእድሜአቸው ተተንትነው ለውሳኔ በሚያመች ሁኔታ ተዘጋጅተዋል፡፡ በተሰጡ አገልግሎቶች ከሚሰበሰቡ ሂሳቦች መካከል፡፡

- አዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን ……….674,05.75
- አፊሌት ተባባሪ …………..201,226.75
- ጎናፍር ትራንስፖርት …………………114,152.73
- ታደሱ በቀለ ………………………137,093.47
- በሌላ በኩል በውል መሠረት የተለያየ አገልግሎት የተሠጠበት ሂሳብ ብር 3,077,223.00 ሲሆን ይህ ሪፖርት እስከቀረበበት ጊዜ ብር 2,701,595.00 ተሰብስቧል፡፡

**ተከፋይ ሂሳቦች**

- ☐ በድርጅቱ ባጠቃላይ ለረዥም አመታት እየተንከባለሉ የመጡና መረጃ ሊገኝላቸው ያልቻሉ በድምሩ ብር 6,487,463.63 ተከፋይ በሌጀር ተመዝግቦ የሚገኝ ሒሳብ ያለ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 5,785,000.00 ከ1986 ከክፍፍል ጊዜ ጀምሮ እየተንከባለለ የመጣና ውሳኔ ያላገኘ የፐሮቪዥን ታክስ ሂሳብ ከፍተኛውን ድርሻ ይዟል፡፡ ይህም ለውሳኔ እንዲረዳ በእድሜ ትንታኔ ተሠርቶ ተዘጋጅቷል፡፡

## የጥሬ ገንዘብ እንቅስቃሴ

- ☐ ድርጅቱ ሥራ ከጀመረ ጀምሮ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ብር 120,000,000.00 የተለቀቀ ሲሆን በድርጅቱ የተገኙ ገቢዎችን ጭምር በመጠቀም ለሥራ ማስኬጃ ወጪ በማድረግ Dec 31 ቀን 2015 ብር 14,928,562.06 በባንክ ሂሣባችን ላይ ይገኛል፡፡

## የትርፍና ኪሳራ መግለጫ

- ☐ ደርጅቱ አዲስ በመሆኑና ገቢ በሚያስገኙ ስራዎች ላይ በበቂ ሁኔታ የገባ ባለመሆኑ በመንፈቅ ዓመቱ 42,249,775.00 ኪሳራ ያቀደ ሲሆን በተጨባጭ የታየው ኪሲራ ግን 86,426,359.00 ሲሆን የከተማ ትራንስፖርት አገልግሎት ማካካሻ ሊሰበሰብ የታቀደው የስድስት ወር የአገልግሎት ማካካሻ 57,500,000 ብር መሰበሰብ ቢቻል የተመዘገበውን ኪሳራ ወደ 28,926 359ብር ዝቅ ማድረግ ይቻል ነበር ሲሆን እንደ አጠቃላይ ለተስተዋለው ኪሳራ መጠን የሚከተሉት እንደምክንያትነት ተጠቅሰዋል፡፡
  - ✓ የአውቶቡሶች የእርጅና ቅናሽ ከፍተኛ መሆን፣
  - ✓ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት በሚፈለገው ደረጃ አለመሠራቱ፣
  - ✓ የኪሳራ ማካካሻ እንዲሆን ለድጐማ የተያዘው አለመሠብሠቡ ናቸው፡፡

## የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ

አንድ የተደራጀ የዳታ ሴንተር በመገንባት በአይ- ቲ- ኤስ ቴክኖሎጂ/ ITS/ የታገዘ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት በእቅድ የተያዘ ሲሆን የሚከተሉት ስራዎች ተከናውነዋል፡

- ☐ እንደመጀመርያ ፌዝ በ200 አውቶብሶች ላይ የ ITS መሳሪያዎች ለመግጠም ታቅዶ በ177 አውቶብሶች ላይ የITS መሳሪያዎች ማለትም MDVR, Camera, ካርድ ሪደር ፣ዳታ ዲስፕሌይ እና ሲም ካርድ ተገጥሞላቸው የኮንፊጌሬሽንም ስራ ተሰርቷል፡፡
- ☐ ዳታ ሴንተሩ የተሟላ እንዲሆን የሚያስፈልጉ እቃዎች ማለትም 6 ሰርቨር ፣ 1 ዳታ ስቶሬጅ ፣ 2 ኤር ኮንዲሽኒንግ ፣ 1 Firewall , 4 Switchs , 1 core Switch ፣1 Router, 8 Access point ፣ 2 የእሳት ማጥፊያ ፣ 4 የቴሌቪዥን እስክሪን ተገጥሟል፣ 8 LED ስክሪን፣ የኤሌክትሪክ መስመር ተስተካክሏል በተጨማሪም ጀነሬተር አውቶማቲክ እንዲሰራ ተደርጓል፡፡
- ☐ Public IP Address ተገዝቶ ከሲስተሙ ጋር እንዲሰራ ተደርጓል፡፡
- ☐ ወደ ዳታ ሴንተሩ ለመግባት ያስችል ዘንድ በአሻራ የሚሰራውን መሳሪያ ተገጥሞ በሙከራ ላይ ይገኛል፡፡
- ☐ ዳታሴንተሩን፣ ፕሪንት ክፍሉንና የኮንትሮል ክፍሉን የሚቆጣጠሩ ሁለት ካሜራዎች ከውጪና ከውስጥ ተገጥመዋል፡፡
- ☐ በአንድ መኪና ላይ የኤሌክትሮኒክስ መታወቂያው እንዲሰራ ሙከራ በማድረግና የITS መሳሪያዎች የተገጠመላቸው መኪናዎችን በሮውስጥ በመሆን መቆጣጠር እንደሚቻል በተቋማችን አመራሮች ታይቷል፡፡

### በዲፖ ግንባታ ዙርያ ተከናወኑ ተግባራት

በበጀት አመቱ በ አራቱም የ አገልግሎት መስጫ ቅርንጫፎች የተደራጀ የዲፖ ግንባታ ለማካሄድ በእቅድ የተያዘ ሲሆን በግማሽ አመት ውስጥ የታየው አፈጻጸም ለግንባታ የሚውሉ ይዞታዎች በወቅቱ ባለመገኘታቸው ምክንያት ዝቅ ቢልም የሚከተሉት የዝግጅት ተግባራትን ማካወን ተችሏል፡፡

- ☐ ለዲፖ ግንባታ የሚውሉ ይዞታዎችን የመረከብ ስራ መስራት የተቻለ ሲሆን በሰሜን፣ ለበምስራቅ እንዲሁም በምዕራብ ለሚከናወኑ የዲፖ ግንባታ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ርክክብ ተደርጓል፡፡
- ☐ በደቡብ አገልግሎት መስጫ ቅርንጫፍ በዲፖ ግንባታ የወሰን አጥር የታጠረ ሲሆን ይዞታውን ከማስፋት ረገድ ተጨማሪ ይዞታ ለማግኘት ጥያቄን ቀርቦ ክትትል በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡
- ☐ የጃን ሜዳ የመኪኖች ማቆሚያ ቦታ የማሰደልደል ሰራ ተሰርቶዋል፡፡
- ☐ ለዲፖ ግባታ ዲዛይን ስራ ይረዳ ዘንድ የቦታ አቀማመጥ / (Topography) ለማወቅ የቅየሳ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡
- ☐ ከኮንሰስትራክሽንና ዲዛይን ጋር ዲዛይን የማማከርና የዲዛይን አገልግሎት ለማግኘት ውል የመዋዋል ስራ ተሰርቷል

### <u>የሥርአተ ጾታና ማህበራዊ ጉዳዮች</u>

| እቅድ | ክንውን |
|---|---|
| የሴቶችና ወጣቶችን ተሳትፎን ባማከለና በቅጥር በመመሪያው መሠረት ቅጥር መፈፀሙን ክትትል ማድረግ፤ | በድርጅቱ የሚካሄዱ ቅጥሮች በመመሪያው መሠረት መፈፀሙንና ሴቶች ተጠቃሚ መሆናቸውን የመከታተልና የማረጋገጥ ሥራ ተሰርቷል፡፡ |
| የትራንስፖርት አገልግሎቱ ለአካል ጉዳተኞች እና ልዩ ትኩረት የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ የሚያደርግ መሆኑን መከታተል፣ | የፐብሊክ ትራንስፖርት አገልግሎት ለአካል ጉዳተኞች የተመቻቸ ለማድረግ በብረታብረትና ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን እንዲዘጋጁ ከተደረጉት 15 አውቶብሶች ውስጥ 1 አውቶብስ ተዘጋጅቶ የቀረበ ሲሆን ይህንንም አውቶብስ በመፈተሽ ማስተካካዮች እንዲደረግበት ማድረግ ከማድረግ ረገድ ክትትል እየተደረገ ይገኛል፡፡ |
| በትራንስፖርት አገልግሎቱ ሴቶችና ወጣቶችን ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፣ | የትራንስፖርት አገልግሎቱ ሴቶችና ወጣቶችን ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ያረጋገጠ መሆኑን በተለያየ መስመር በተሰማሩ 4 አውቶቡሶች ላይ በተደረገ ቃለመጠይቅ የማረጋገጥ ሥራ ተሰርቷል፡፡ |

| እቅድ | ክንውን |
|---|---|
| በሚዘጋጁ መመሪያዎችና ደንቦች ሴቶችና ወጣቶችን ተጠቃሚነት አንጻር ክፍተቶችን በመለየት እንዲስተካከሉ ግብዓት የመስጠትስራ መስራት | በተዘጋጁ የሥራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብ ላይ እና የድርጅቱ ረቂቅ ሕብረት ስምምነት ላይ የሴቶችን ጉዳይ ያካተተ እንዲሆን ግብአት የመስጠት ስራ ተሰርቷል ። |
| ሴቶችና ወጣቶች በሚመለከት በሚዘጋጅ ፎረሞች የአሰራር ልምዶችንና ተሞክሮዎችን መቅሰም። | በትራንስፖርት ሚኒስቴር የሴቶች ቢሮ በተጠራ የ2007 ዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ እና የ2008 ዕቅድ ላይ በጋራ ለማቀድ ስብሰባ ላይ ተሳትፎ ማድረግና እንደ ትራንስፖርት ሚኒስቴር የፎረም አባል መሆን ተችሏል። |
| ሴቶች በራስ መተማመናቸውን ለማሳደግ የተለያዩ አጫጭር ስልጠናዎችን በውጭ አሠልጣኝ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ። | በድርጅቱ ውስጥ ያሉ 65 የሚሆኑ ሴት ሠራተኞች ስለ ሥርዓተ ፆታ ግንዛቤ እና በአንስተኛና ጥቃቅን የብድር አገልግሎት ለማግኘት የሚያስችል ሥልጠና በሁለት ቀን ተሰጥቷል። በሥልጠናው ወቅት መጠየቅ በመበተን ግብረመልስ ተሰብስቦ ሪፖርት ተደርጓል። |
| የኤች አይ ቪ ኤድስ ቀንን በማስመልከት በድርጅቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ የውይይት መድረክ ማዘጋጀት | የኤድስ ቀን በማስመልከት የተዘጋጀ በድርጅቱ ግቢ ውስጥ 34 ሴቶች እና 77 ወንዶች በድምሩ 111 ሠራተኞች በውይይት መድረክ እንዲገ ማድረግ በዓሉን በደመቀ ሁኔታ እንዲከበር ተደርጓል። |

## የኮሙኒኬሽን ሥራዎች

| እቅድ | ክንውን |
|---|---|
| በቴሌቪዥን በሬዲዮ እና በጋዜጣ ለህዘቡ መረጃዎች ለህብረተሰቡ እንዲደርሱ የማድረግ ስራ ማከናወን፣ | የተለያዩ የመገናኛ ብዙኃን በመጠቀም የድርጅቱ ኃላፊዎች አገልግሎቱን ተደራሽ ለማድረግና ድርጅቱ እየሰራ ያለውን የለውጥ እንቅስቃሴ ህዝቡ እንዲገነዘብ በመገናኛ ብዙኃን እንዲገለፅ ተደርጓል፡፡በዚህ መሰረት አጠቃላይ ስድስት ወር ውስጥ 22 ዜናዋችን በመገናኛ ብዙሀን ለህዝብ ማድረስ ችሏል፡፡ |
| የድርጅቱን አንደኛ ዓመት ምስረታ በዓል አከባበር አስመልቶ ድርጅቱን በተሻለ መልኩ ለማስተዋወቅ ይቻል ዘንድ መጽሔት አዘጋጅቶ ለህዝብ ክንፉ ማሰራጨት፣ | የድርጅቱን የአንድ ዓመት ጉዞ ሚያሳይ የቦርድ አባላትና የድርጅቱን ኃላፊዎች እንዲሁም የተጠቃሚውን አስተያት ያካተተ 48 ገፅ ያለው 2000 መፅሔት በማሳተም በተለያዩ የስብሰባ እና የህዝብ ክነፍ መድረክ ላይ የማሰራጨት ስራ መስራት ተችሏል፡፡ |
| የተለያዩ መገናኛ ብዙኃንን በመጠቀም በድርጅቱ ላይ ለሚሰነዘሩ አስተያየቶችና ማብራሪያ በሚፈልጉ ጉዳዮች ላይ ምላሽ መስጠት፣ | በአገልግሎቱ ዙሪያ ከተጠቃሚ የሚነሱ ጥያቄዎችንና ቅሬታዎችን በኤፍ ኤም ሬዲዮኖችና በዜና አገልግሎት እንዲሁም በአዲስ ዘመን ጋዜጣ በኃላፊዎች ምላሽ እንዲሰጥበት ተደርጎ ለህዝብ እንዲደርስ ተደርጓል፡፡<br>በዚህም በኤፍ ኤም አዲስ 97.1 ለሁለት ሰዓታት ቆይታ ባለው መልኩ በቀጥታ ስርጭት ከተጠቃሚዎች ለሚነሱ ጥያቄዎች በድርጅቱ ስራ አስኪያጅና በትራንስፖርት ኦፕሬሽን ሃላፊዎች በሚነሱ ጥያቄዎች ምላሽ እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡ |
| ህዝበዊ ባአላትን መሰረት በማድረግ የድርጅቱን በተሻለ የማስተዋወቅ ስራዎች ማከናወን፣ | የገናን በዓል አስመልክተን በኢቢሲ 1 እና በፋና ሬዲዮ ተጠቃሚዎቻችን እንኳን አደረሳችሁ ከማለታችን ባሻገር ድርጅታችን ለከተማው ህዝብ እየሰጠ ያለውን የታክሲ አገልግሎት በተመለከተ ማስታወቂያ ተዘጋጅቶ በበዓሉ ዋዜማና ዕለት በተደጋጋሚ እንዲተላለፍ በማድረግ የግንዛቤ ስራ ተሰርቷል፡፡ |
| ከትራንስፖርት ሚንስቴር መንግስት እንዲሁም ኮሙዩኒኬሽን አባላት ጋር ተቀናጅቶ በመስራት የኮሙዩኒኬሽን ስረዎችን ማከናወን | በመልካም አስተዳደር ዙሪያ በትራንስፖርት ሚንስቴር እና በኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት የተሰጡ ስልጠናዎችን ፣በመልካም አስተዳደር ዙርያ በተቀቀምው ኮማንድ ፖስት ፣ በተለያዩ ስብሰባዎችና ግንዛቤ ማስጨበጫዎች ላይ በመሳተፍ የኮኒከሼን ሚና የማከናወን ስራ ተሰርቷል |

በእቅድ ተይዘው ያልተካናወኑ ዋናዋና ተግባራት

- በአራቱ ቅርንጫፎች የተደራጀ የዲፖ ግንባታ ማካሄድ፣
  - የዲፖ ግንባታ  በታቀደው ፕሮግራም ያለተከናወነ ሲሆን ለዚህም በማኬድ ሊገነቡ የታቀዱ ዲፖዎች በወቅቱ ያለመካናወን  አብይ ምክንያት ለግንባታ የሚውሉ ይዞታዎች በወቅቱ ማግኘት ባለመቻል ምክንያት ነው፡፡

- የኢንተለጀንት ትራንስፖት ሲስተም/ITS/ በሁሉም አውቶብሶች ላይ በመግጠም ተግባራዊ ማድረግ፡፡
  - የኢንተለጀንት ትራንስፖርት ሲስተም በታቀደው መሰረት ተግባራዊ መሆን ያልቻለው ከብረታብረትና እና ኢንጂነሪን ኮርፖሬሽን ቢሾፍቱ አውቶሞቲቭ እንደስትሪ ጋር ባላ የስራ ውል መዘግየት ምክያት ነው፡፡

## በእቅድ አተገባበር ወቅት የነበሩ ጠንካራና ደካማ ጎኖች

| | |
|---|---|
| **ከፍተኛ አመራር** | |
| **ጠንካራ ጎን**<br>1. ከእቅድ ዝግጅት እስከ አተገባበር ክትትልና ግምገማ የሚያደርገው ጥረት<br>2. የለውጥ ስራዎች ላይ ትኩረት ሰቶ መንቀሳቀስ<br>3. ስራን በለውጥ ሰራዊት አደረጃጀት ለመመምራት ቁርጠኝነት መኖሩ<br>4. ለወቅታዊ መልካም አስተዳደር ንቅናቄ ፈጣን ፈጣን ምላሽ ለመስጠት የሚደረግ ጥረት<br>5. በመካከለኛ አመራሩ ጋር ባለ ስራ ግኑንነት ግልጽነትና ሃሳብን በነጻነት የማሰሸራሸር ልምድ እንዲዳብር ጥረት መደረጉ<br>6. የአውቶብስ ካፕቴኖችን አቅም ለመገንባት የሚደረግ ጥረት | **ደካማ ጎን**<br>1. የማስፈፀም አቅም ውስንነት፣<br>2. የአመራር ቁርጠኛነት በተፈለገው መልኩ አለመዳበር፣<br>3. በቅንጅት የመስራት ውስንነት፣<br>4. የክትትልና የግምገማ ስርዓት አጠናክሮ ከመሄድ አንጻር ክፍተት መኖሩ<br>5. ተተኪን ማዘጋጀትና የማብቃት ጋር በተያያዘ ክፍተት መኖሩ፣ |
| **መካከለኛ አመራር** | |
| **ጠንካራ ጎን**<br>1. በለውጥ ሰራዊት አዳደራጅቶ ከመምራት ረገድ ያላቸው ጥረት<br>2. ስራን በቡድን ለመስራት የሚደረግ ጥረት መኖሩ<br>3. የክትትልና ቁጥጥር ስራዎች ረገድ ያለው እንቅስቃሴ | **ደካማ ጎን**<br>1. እርምጃ ለመውሰድ የውሳኔ ቁርጠኝነት አለመኖር<br>2. በተወሰኑ አካላት የሚስተዋል የክትትልና ድጋፍ ውስንነት መኖሩ<br>3. ቁርጠኝነትና በውጤት ላይ የተመሰረተ ስራን ከመስራት ረገድ ክፍተት መኖሩ<br>4. ስራዎችን በቡድን ከመስራት ረገድ በተወሰነ መልኩ ክፍተት መኖሩ<br>5. በተወሰነ መልኩ የሚወርዱ መመርያዎችን በተፈለገው መልኩ አለመተግበር |
| **አጠቃላይ ፈጻሚው** | |
| **ጠንካራ ጎን**<br>1. በለውጥ ሰራዊት ቡድን አደራጅት ያላቸው ተሳትፎ<br>2. ለስልጠና እና በእውቀት ሽግግር እራሳቸውን ለማዳበር ፍላጎት መኖሩ<br>3. ሃላፊነትን ለመወጣት ጥሩ በሚባል ደረጃ የሰራተኞች ተነሳሽነት መኖሩ | **ደካማ ጎን**<br>1. የተቀመጡ አሰራሮችን በተገቢው መልኩ ያለመተግበር<br>2. የበላይ አካል ጠባቂነት አዝማምያ መኖሩ<br>3. በሚፈለገው ደረጃ ሃላፊነትን ያለመወጣት<br>4. የሚሰጡ ስልጠናዎችን ወደ ተግባር ከማውረድ ረገድ ክፍተት መኖሩ<br>5. ችግሮችን በውይይት የመፍታት ባህል አለመዳበር |

| ግንባር ቀደም ፈጻሚው | |
|---|---|
| ጠንካራ ጎን | ደካማ ጎን |
| 1. መመርያና ደንብ በሚፈቅድ መልኩ መደራጀታቸው<br>2. የተለዩት ግንባር ቀደም አባላት ያላቸው ተነሳሽነት<br>3. በግንባር ቀደም ሚና ዙርያ ለሁሉም ግንባር ቀደሞች ስልጠና መሰጠቱ | 1. ግንባር ቀደሙ በሚፈለገው መልኩ ውጤት አለማምጣቱ |
| ህዝብ ክንፍ | 2. |
| ጠንካራ ጎን<br>1. የተለዩት ህዝብ ክንፍ በድርጅቱ እንቅስቃሴ የሚያሳዩት ተሳትፎ<br>2. በህዝብ ክንፍ ለተነሱ ችግሮች እና ለተወሰዱ ማሻሻያዎች ለህዝብ ክንፉ ግልጽ የማድረግ ስረ መስራታቸው፣<br>3. ህዝብ ክንፉ በቋሚነት በሚፈጠሩ መድረኮች ላይ መሳተፍ መቻላቸው፣<br>4. ከህዝብ ክንፉ ጋር በጋራ በመስራት ለውጦችን ማምጣት ሁኔታዎች መኖራቸው፣<br>5. በአብዛኞቹ በጋራ በሚወሰዱ አቋሞች ላይ ያለ ቁርጠኝነት | ደካማ ጎን<br>1. በተወሰኑ ህዝብ ክንፍ የኮሚትመንት ክፍተት መኖሩ፣<br>2. በስብሰባዎች ላይ ተገቢው ተወካይ ያለመቅረብ<br>3. የተወሰኑ የህዝብ ክንፍ አካላት የማስተባበር ስራ ላይ ውስንነት መኖሩ፣<br>4. የሚወርዱ መመርያዎችን በተገቢው መልኩ አለመተግበር |

## ያጋጠሙ ችግሮችና መፍትሄዎቻቸው

| ተ.ቁ. | ያጋጠሙ ችግሮች | የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች | ሊወሰዱ የሚገባቸው የመፍትሄ እርምጃዎች |
|---|---|---|---|
| 1 | የአውቶብስ ማዋያና ማደርያ ስፍራ ፣የራሳችን የሆነ የነዳጅ ማደያና ሌሎች ፋሲሊቲዎች ያለመኖር | የአውቶብስ ማዋያና ማደርያ ስፍራ ፣ የነዳጅ ማደያና ሌሎች ፋሲሊቲዎች በተመለከተ ያሉ ችግሮችን በተቻለ መጠን ለመፍታት ጥረት የማድረግ ስራዎች በማከናወን ላይ ናቸው :: | እየተደረጉ ያሉ ጥረቶችን አጠናክሮ በማስቀጠል ጊዜ ሳይሰጠው ችግሮችን ለመፍታት ጥረት ማድረግ :: |
| 2 | በጎማ ዓይነትና ጥራት ምክንያት የመንገድ ላይ ብልሽት መብዛት | የመከላከል ጥገናው ላይ ክትትል በማድረግ ችግሩን ለመቀነስ እየተሞከረ ይገኛል። የችግሩ መንስኤ ሊሆኑ የሚችሉ ምክንያቶችን የመለየት ስራ ተሰርቷል። | ችግሩን ከ ጎማ አቅራቢዎች ጋር በመወያየት ለመፍታት ጥረት ማድረግ። |
| 3 | ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር መሰብሰብ ያለበትን ሂሳብ በተለያዩ ምክንያት አለመሠብሰብ፣ | ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመወያየት ችግሩን ለመቅረፍ ጥረት ቢደረግም አፋጣኝ ውሳኔ ማግኘት አልተቻለም። | የተጀመረውን ጥረት አጠናክሮ በማስቀጠል ክፍያዎች እንዲሰበሰቡ እና ለወደፊት ወጥ የሆነ አሰራር እንዲኖር የማድረግ ስራ መስራት |
| 4 | ለኪሳራ ማካካሻ ይገኛል ተብሎ ለድጉማ የተያዘው እቅድ አለመሰብሰቡ፣ | ችግሩን ለመፍታት ኮሚቴ ተቋቋሞ ባቀረበው የውሳኔ ሀሳብ መሰረት የመጨረሻ ውሳኔ እየተጠበቀ ይገኛል፡፡ | ጉዳዩ ቶሎ ውሳኔ እንዲያገኝ የክትትል ስራን በተሻለ መልኩ ማጠናከር |
| 5 | የኢንተለጀንት ትራንስፖርት ሲስተም /ITS/ ስራ በሚፈለገው ጊዜ በቶሎ አለመጠናቀቁና በእቅዶቻችን ላይ ችግር መፍጠሩ፡፡ | ከተቋራጩ ጋር በየጊዜው በመገናኘት ውይይት ባመድረግ ስራዎች በአፋጣኝ በሚያልቁበት ሁኔታዎች ላይ ረት ተደርጓል፡፡ | እየተደረገ ያለው ጥረት እንደቀጠለ ሆኖ የሚደረጉ ጥረቶችን፣የደረሰበትን ደረጃ እንዲሁም ከአቅም በላይ የሆኑ ጉዳዮችበወቅቱ ለሚኒስቴር መስርያቤቱ ማሳወቅ፡፡ |
| 6 | የመገልገያዎች አቅርቦት ችግር | የአቅርቦት ችግርን በማስመልከት በአንድ ለአምስት ውይይትና በማኔጅመንት ስብሰባ ላይ ግዥዎች ወቅታቸውን እና ጥራታቸውን ጠብቀው እንዲቀርቡ ውሳኔዎች እና ክትትሎች ደርገዋል። | የድርጅቱ መልካም አስተዳደር ችግር ሆኖ እስከመቅረብ የደረሰ በመሆኑ አቅርቦትን ቀልጣፋና ወቅታዊ ማድረግ‹‹ |

## <u>በቀጣይ ስድስት ወራት ትኩረት የሚደረግባቸው ጉዳዮች</u>

- የመልካም አስተዳደር የንቅናቄ እግቅድ አፈጻጸምን አጠናክሮ የማስቀጠል ስራ መስራት፣
- በለውጥ ስራዎች የሚከናወኑ ተግባራትን አጠናክረ ማስቀጠል፣
- አጠቃላይ አወቶብሶች እንዲገቡ ክትትል በማድረግ ትራንስፖርት አገልግሎት ተደራሽነትን ማሳደግ፣
- በሁሉም ቅርንጫፍ የዲፖ ግንባታ ስራዎችን አጠናክሮ መስራት ፣
- ኢንተለጀንት ትራንስፖርት ሲስተም /ITS/ ስራዎችን አጠናክሮ በማስቀጠል ተግባራዊ ማድረግ፣
- በትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ዙርያ ዳሰሳ ጥናቶችን በማካሄድ በአገልግሎት አሰጣጥ የሚታዩ ክፍተቶችን ማስተካከል፣